# በዓሉን የበላ ጅብ!

ታሪኩ አባዳማ ሐምሌ 2006

ዘለግ ላሉ ዘመናት የማውቀው አበራ ለማ በቅርቡ 'በዓሉን የበሉ ጅቦች' የሚል አስራ ስድስት ገፅ ሀተታ አስነብቦናል። ይህ በሆነ ጥቂት ቀናት ፅሁፋንም ፀሀፊውንም የሚመለከት የተለያየ አስተያየት ተሰንዝሯል። በአበራ ፅሁፍ ቅር የተሰኙ አንዳንድ ወገኖች ሰውየው ወደ ወያኔ ሰፈር መቀላቀሉን ይፋ አደረገ ሲሉ ፣ ሌሎች ደግሞ በፅሁፉ የተነሳው አብይ ጉዳይ መልስ እንደሚያስፈልገው ሀሳብ ሰንዝረዋል። 'በዓሉን የበሉ ጅቦች' መኖራቸውን አበራ መጠቆሙ 'መብቱ' ነው ስለዚህ ስማቸው የተነሳ ሰዎች መልስ ሊሰጡ ይገባል የሚሉ። ሁለቱም አስተያየት ሰጭዎች የሚፃረሩ ይምሰሉ እንጂ በይዘታቸው ተመሳሳይነት አላቸው - ጠለቅ ብሎ ነገርን አለማገናዘብ እና ከቧልት መንደርደሪያ ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ መድረስ ሁለቱም ወገኖች ላይ ተንፀባርቋል። ለነኝህ ስህተቶች መፈጠር ዋና ተጠያቂው ግን አበራ ያቀረበው መጣጥፍ ነው… ምክንያቱን አስረዳለሁ።

አበራ ከወጣትነት ዘመኑ ጀምሮ ተሰጥኦ ያለው ገጣሚ እና ፀሀፊ ነው። ያኔ በወጣትነት ዘመኑ ተሰጥኦውን ሙሉ ለሙሉ የሚያበለፅግበት አመቺ መድረክ ያገኘ ግን አይመስለኝም። ተሰጥኦ ያላቸው እንደ አበራ ለማ ያሉ ዜጎች ራሳቸው ተፍጨርጭረው መሰናክሎችን አልፈው ካልሆነ በስተቀር እንደ ምዕራቡ አለም በተወሰነ ሙያ ዘርፍ ተሰጥኦ talent ያለውን ወጣት ልዩ ድጋፍ ሰጥቶ የሚከባከብ ባህል ሆነ ስርዓት ዛሬም ቢሆን የለንም። ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ማለት ቢቻልም የዚህ ፅሁፍ አላማ ሌላ በመሆኑ አልፈዋለሁ።

አስቀድሜ ግን አበራ ስለ አገሩ ሆነ ህዝቡ ያለውን ጠንካራ ስሜት በደንብ በቅርብ ስለማውቅ ዛሬ ስልጣን ላይ ካለው ዘረኛ እና ፀረ-አገር ወያኔ ጎራ ይሰለፋል ተብሎ የሚጠረጠር ሰው አለመሆኑን መጥቀስ ተገቢ ነው። ለመሆንም የሚያስገድደው ሰበብ አይታየኝም። ይሁንና ያቀረበው ሀተታ ሰዎችን ወደ ተዛባ ድምዳሜ ቢገፋ አለምክንያት አይመሰለኝም። ስለሆነም ነገሮችን መስመር ያስይዛል በሚል ግምት ፅሁፋን በሌላ እይታ ልቃኝ ተነሳሁ። ይህን መጣጥፍ ላቅርብ አላቅርብ ብዬ ከራሴ ጋራ ለቀናት ስሟገት መቆየቴን ከወዲሁ ላነሳ ወዳለሁ።

አበራ በሀተታው ነገርን ከነገር እያስታከከ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በቆየባቸው ዓመታት በእርሱ እና ባልደረቦቹ ላይ ደረሰ ያለውን በደል በምሬት ቃላት አጅቦ ፅፏል። በዚህ የተነሳ ፅሁፉ 'በዓሉን ስለ በሉት ጅቦች' የደረሰበትን ጠቋሚ ጭብጥ ከመተንተን ይልቅ ፈሩን ስቶ እሱ ጋዜጠኛ በነበረበት ወቅት በደል ፈፅመውብኛል ብሎ በፈረጃቸው ግለሰቦች (አቶ ሙሉጌታ ሉሌን ጨምሮ) ላይ ያነጣጠረ እርግማን እና ውረፋ ላይ ተጠምዶ ከመደምደሚያው ደርሷል። ይህ አስራ ስድስት ገፅ ሀተታ ሁለት ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ ከቶ የማይቀራረቡ ጉዳዮችን ለማዛመድ እና በመቼት የማይመሳሰሉ ፋይሎችን እያሳለጠ አንዱን ካንዱ ለማምታታት የሞከረ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። አበራ የቆየ ብሶቱን አደባባይ ለማውጣት ሲል የግል ጉዳዩን ከበዓሉ ግድያ ጋር አዳብሎ ለማቅረብ መሞከሩ ትልቅ ስህተት ነው። የዚህ አይነቱ አቀራረብ ሌሎች ስለ አበራ ያላቸው ግምት እንዲጣመም ምክንያተ ሆኗል።

በፅሁፉ አበራ ያቀረበው ጉዳይ ማለትም 'በዓሉን የበሉ ጅቦች' አልጮህ አሉ የሚለው አቀራረብ ከቶውንም በዓሉን ማን እንደበላው ምስጢር ሆኖ እንደተዳፈነ የቀረ ያህል በመቆርቆር የቀረበ ይመስላል። ለበዓሉ መሰወር እና መጥፋት ቀጥተኛ ተጠያቂ የሆነውን ደርግ ወደ ጎን አስቀምጦ ሌሎች ግለሰቦችን ለማነካካት የተደረገ ሀላፊነት የጎደለው አሉባልታ መሆኑን አላንዳች ይሉኝታ መናገር ይቻላል። ደርግ በጭለማ ሊበላህ ሲፈልግ ፍየል ወጠጤ ብሎ አይጮህም - ዋጥ ስልቅጥ አድርጎ ጭጭ ፍጥጥ ነው። ወዳጅ ዘመዱ በሀዘን እህህ እያለ ፣ የባጥ የቆጡን እየጠረጠረ ይኖራል። ወያኔም እቺን ስልት ጥሩ አድርጎ ይጠቀምባታል።

አበራ በርዕሱ እና መግቢው ላይ 'በዓሉ ግርማን ማን ገደለው'? ለሚለው ጥያቄ ጉዳዩ 'እንግዳ' እንደሆነ ሁሉ አዲስ ጭብጥ ይዞ የቀረበ በሚመስል አካሁዋን ይንደረደራል። የበዓሉ ጓደኛ የነበረው አስፋው ዳምጤ አብሮ ለማምሸት ጋብዞት እንደወጣ ቀረ ይለናል። ዝቅ ይልና ሙሉጌታ ሉሌን በግድያ ሴራው እንደተሳተፈ የሚያስጠረጥር ነገር እንዳለ ይጠቁማል። እነኝህ ሁለት 'ተጠርጣሪዎች' በዓሉ እንዲጠፋ የሚሹበትን ሞቲቭ አበራ ሲጠቅስ አስፋው ስራ ፈት ስነለበር ስራ ፍለጋ ፣ አቶ ሙሉጌታ ደግሞ የበዓሉን ወንበር ስለተመኘ መሆኑን ይጠቅሳል። እውን እነኝህ ግለሰቦች ለዚህ ለተባለ ነገር ሲሉ በማሴራቸው ይሆን በዓሉ ለሞት የተዳረገው? በመሰረቱ አስፋው ዳምጤ በደርግ ዘንድ ሞገስ ለማግኘት ሲል ጓደኛውን ለእርድ አቀረበ ማለት የምንችለው ደርግ በዓሉን ለመግደል ፈልጎ ግን የት እንደሚይዘው ጠፍቶት ሲሆን ብቻ ነው። በዚህ ረገድ በዓሉ ከተደበቀበት እንዲወጣ አስፋውን እንደ ወጥመድ ተጠቀመበት ለማለት እንችል ነበር። በዓሉ የፈፀመው ወንጀል ስለሌለ ከደርግ ይሁን ከማንም ተደብቆ አያውቅም። ኦሮማይን በመፃፉ ከስራው ታግዶ በቆየበት ታፈኖ እስከ ተገደለበት ጊዜ ድረስ ቀድሞውኑ ያዘወትራቸው ከነበረበት የአራዳ ግሮሰሪዎች ብሎም ከአደባባይ ተሰውሮ አያውቅም። እንደ ሁልግዜውም በግልፅ ይታይ ነበር - ከጓደኞቹ ጋር እንደውትሮው ይገናኝ ነበር። ከአስፋው ዳምጤ ጋርም ይገናኙ ነበር። በወቅቱ የታየ አዲስ ነገር ቢኖር የደርግ ደህንነት በዓሉን እግር ለግር እተከታተለ መውጫ መግቢያውን ያጠና እንደ ነበር ብቻ ነው። የአበራ ለማ ሀተታ ይህን የደህንነት ክትትል ደጋግሞ ጠቅሷል። ከአስፋው ዳምጤ

ጋር አዘውትረው እንደሚገናኙ ይህ እግር ለግር የሚከታተለው ደህንነት አያውቅ ይሆን? ደህንነት ያልተደበቀ ሰው እያሳደደ ፣ እየተከታተለ ፣ መውጫ መግቢያውን እያነፈነፈ እኮ ነው። በዓሉ እና የደርግ ደህንነት እንደ ሰስ እና ነብር የሆኑበት ሰሞን። የወያኔ ደህንነት ተመሳሳይ ነገር እንደሚፈፅም ከነ እስክንድር ነጋ ታሪክ ማስታወስ ይቻላል። በገባህበት በወጣህበት በተዘዋወርክበት ሁሉ ሶስት አራት ደህንነት ይከተልሀል - በዓይነ ቁራኛ።

በዓሉ በደህንነት ታፍኖ ሲወሰድ አስፋው ዳምጤ አይቶ ነበር ብንል እንኳ - የተፈፀመውን ስውር አፈና ለሌላ ቢናገር ተመሳሳይ ዕጣ ሊደርስበት እንደሚችል በመፍራት ቤቱ ገብቶ ዝም ቢል የሚፈረድበት አይሆንም። በደርግ ዘመን ለነፍስህ ብትፈራ ይፈረድብሀል? ለማንስ ምን ይነገራል? ለቤተሰቡ ቢናገር ጉዳዩ ይፋ ሆነ ማለት ስለሆነ ብቸኛው አይን ምስክር አስፋው ዳምጤ ጣጣ ውስጥ ሊገባ ነው። አስፋው የነበረው ምርጫ ከበዓሉ ቤተሰብ መራቅ ብቻ ነው። እንደኔ ግምት ከሆነ አስፋው ዳምጤ ከበዓሉ ቤተሰብ መራቁ በተዘዋዋሪ የደረሰበትን የህሊና መረበሽ የሚያመለክት ነው ባይ ነኝ። በነገሬ ላይ አስፋው ዳምጤን በስም እንጂ በአካል አላውቀውም።

በደርግ ዘመን በፀረ-አብዮት ከተጠረጠረ ሰው ጋር ቡና መጠጣት ያቆሙ የቅርብ ጓደኞች እጅግ ብዙ ናቸው። ስለ አስፋው ዳምጤ ሁኔታ ስናይ ግን ጓደኛው በዓሉ በኦሮማይ የተነሳ ከደርግ ጋር ቢላተምም አልሸሸውም ፣ አብሮት ለማምሸት ጭምር አልፈራም። ይሁንና ምሽቱን ደርሶ ባየው ነገር ደንግጧል ፣ ለራሱ ፈርቷል። ይህስ ሆኖ ቢሆን ይፈረድበታል? እናም አስፋው ዳምጤ ከበዓሉ ቤተሰብ ቢሸሽ ነብሱን ለማዳን እንጂ ጓደኛውን በማስበላቱ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ምን ያህል ተቀባይነት ይኖረዋል። አልፎ ተርፎ እንደ ተፈላጊ ወንጀለኛ አዛውንት ፎቶውን ድረ-ገፅ ላይ መስቀል 'ማንም ሰው በህጋዊ ፍርድ ቤት እስካልተበየነበት ድረስ ነፃ ነው' የሚለውን የህጎች ሁሉ ማዕዘን ድንጋይ መርህ መጣስ አይሆንም? በመሰረቱ አስፋው ዳምጤ የበዓሉ ቅርብ ጓደኛ መሆኑ ግልፅ  ሆኖ ሳለ አብረው ማምሸታቸው ለምን እንደ አዲስ ነገር እንደተቆጠረ አይገባኝም።

እውን በዓሉን ማን እንደገደለው አናውቅም? ወይንስ አስፋው ዳምጤ የሚባል ጓደኛው አደባባይ ወጥቶ 'በዓሉን ጎትተው ሲወስዱት አይቻለሁ' ብሎ ካልነገረን በዓሉ በደርግ መገደሉን እንጠራጠራለን?

በሙሉጌታ ሉሌ ላይ የቀረበው ስሞታ ከዚህ የዘለለ አይደለም። ሙሉጌታ ሉሌ የተጠረጠረበት ምክንያት የበዓሉን ወንበር ወይንም ምክትል ሚነስትርነት ቦታ ይመኝ ስለነበረ ነው በማለት አበራ ደጋግሞ ያነሳል። ለመሆኑ አንድ መምሪያ ሀላፊ ምክትል ሚኒስትር ለመሆን ቢመኝ ምኑ ላይ ነው ጥፋቱ? ሁላችንስ ቢሆን ካለንበት እርከን ወደ ላይ ማደግ እንመኝ የለም? አንድ ሰው ወደ ላይ ለማደግ ለመሾም የማይጥር የማይመኝ ቢሆን ይገርመል። ሙሉጌታ ምክትል ሚኒስትር ለመሆን ብቃት አለኝ ብሎ ቢመኝ ጤናማ ዝንባሌ አይደለም? በዓሉስ ሙሉ ሚኒስትር ለመሆን ሳይመኝ ይቀራል? ቢመኝስ እንግዳ እና አስገራሚ ነገር ነው? በስራ ገበታችን ላይ ወደ ላይ ለማደግ መመኘት እንደ ወንጀል ሞቲቭ ተደርጎ መቆጠር የጀመረው ከመቼ ወዲህ ነው?

በጨዋነቱ እና ሰው አክባሪነቱ የማውቀው አበራ እነኝህን ተጠርጣሪ ያላቸውን ሰዎች ሲገልፅ ለምን ተራ ቃላት ለመጠቀም እንደፈለገ ግን ይገርመኛል። ለምንስ ሙሉጌታ ሉሌ ስለ ራስ መስፍን ስለሺ ድህነት የፃፈውን አሮጌ ሀተታ ለመምዘዝ መረጠ? ለምንስ ብዙ ተሞክሮዎችን ለዛሬው ትውልድ ለማካፈል የሚበቁ ወቅታዊ የሙሉጌታ ሉሌን ሀተታዎችን በቁሙ ለመዝለፍ ተጋበዘ? አበራ ለምን ወደ ግል ዘለፋ እንዳዘነበለ ለመገመት ቢያዳግተኝም የዛሬ ሰላሳ ዓመት የደረሰበት ከስራ መባረር ብሶት ህሊናው ላይ የፈጠረው ጠባሳ ዛሬ ድረስ እንዳልሻረ ይህም እንደ ሙለጌታ ሉሌ ባሉ የቀድሞ አለቆቹ ላይ ያደረበትን ቂም ለመወጣት መነሳቱን የሚያመለክት ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ቂም በቀሉ አለቦታው በመቀመጡ ግን በጎ ያልሆነ ግምት ላይ የጣለው ይመስለኛል።

አበራ እንደሚለው ገዳሙ አብረሀ የሚባል 'ለሻቢያ እና ጀበሀ' የሚሰራ መምሪያ ሀላፊ እሱንና ጓደኞቹን ከስራ አንዳባረረ ፣ ሙሉጌታ ሉሌ ደግሞ የገዳሙ ጓደኛ እና የቅርብ ረዳት ስለነበር ብቻ በጠላትነት ይፈርጀዋል። በመሰረቱ ሻቢያና ጀበሀ አጥፊና ጠፊ ስለነበሩ ገዳሙ ለሁለቱም አገልጋይ የሚሆንበት አጋጣሚ የለም።

ማነው አበራን እና ሌሎቹን ጋዜጠኞች ከስራ ያባረረው? ጥያቄውን ለመመለስ እንዳደንድ ነገር ማንሳት ሊኖርብኝ ነው። ለግንዛቤ ያህል ወደ ሁዋላ ሄደን ከ1969 የፖለቲካ ትኩሳት እስከ ደርግ ሰደድ (ኢሰፓ) ፓርቲ ምስረታ ድረስ የነበሩ ጉዳዮችን በጣም በአጭሩ ለመቃቀስ እገደዳለሁ። ያንን ወቅት የሚያብራሩ አያሌ መፅሀፍት ስላሉ እዚህ አንባቢን በዝባዝንኬ አላሰለችም።

የደርግ/ኢሰፓ ፓርቲ ምስረታ እንዲሳካ 'የመኢሶንና አህኢፓ ርዝራዦች ከህዝብ ማህበራት እና ቁልፍ ቦታዎች ሁሉ እንዲመነጠሩ' ሲል ደርግ በ 1970 መጨረሻ ግድም ያወጣውን የውስጥ መመሪያ ልብ ይሏል። ይህን የውስጥ ምንጠራ በሚመለከት የደርጉ እና ሰደድ አውራ ካድሬ የነበረው ገስጥ ተጫኔ 'ነበር' በሚል ርዕስ ባሳተመው መፀሀፉ በሰፊው አትቷል። በዚህ የምንጠራ ዘመቻ ከስራ ገበታቸው የተባረሩ ፣ የተገደሉ እና እስር ቤት ከለ አንዳች ክስ ለዓመታት የማቀቁ የተጠረጠሩ 'የመኢሶንና ኢህአፓ' ደጋፊዎች በአሰርት ሺህ የሚቆጠሩ እንደነበሩ አበራ የሚስተው አይመስለኝም።

በዚያን ሰሞን ትታሰራለህ ግን ለምን እንደታሰርክ የሚነግርህ የለም፣ ከስራ ትታገዳለህ ግን አንዳችም ህጋዊ ስርዓት የተከተለ ምክንያት አይነገርህም ፣ ኢህአፓ የከተማ ግድያ ባቆመበት በዚያ ወቅት ኢህአፓ ገደለው ተብሎ ጋዜጣ ላይ ይታወጃል - የዶር መኮንን ጆቴን እና አብዱላሂ ዩሱፍን ግድያ ለአብነት መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል። ይህ ሁሉ ግፍ ይፈፀም የነበረው ሰደድ የተባለው የደርግ ፓርቲ ያለ እንከን ኢሰፓ ፓርቲውን እንዲመሰርት ነበር። ደርግ 'መኢሶንና ኢህአፓን ሲመነጥር' ወያኔ እና ሻቢያ በውስጡ ለመሰግሰግ መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸው እንደነበር አይካድም። 'ተላላኪው ጋዜጠኛ' በሚል ርዕስ ከዚህ ቀደም ያቀረብኩትን ፅሁፍ የምታስታውሱ … ዝርዝሩ ያንገሽግሻል።

እንደ አበራ አባባል እሱንና ባልደረቦቹን ከስራ ያገደው ገዳሙ የሚባል መምሪያ ሀላፊ ነው። ይሁንና እነ አበራ በጊዜው ተራማጅ ተብሎ ከሚጠራ የፖለቲካ ድርጅት ጋር 'ንክኪ' እንደነበራቸው ከስራ የመታገዳቸው ቁልፍም ከዚህ ጋር የተቆራኘ መሆኑን አበራ በዚህ ፅሁፉ ባያነሳውም ሁሉም ጋዜጠኛ ያውቃል። ገዳሙ ደግሞ (የወቅቱን አገላለፅ ለመጠቀም) እንደ ብዙዎቹ የደርግ ቢሮክራቶች ጭልጥ ያለ አድህሪ ነበር። እነ አበራን ቢችል በሱ መዳፍ ስር አድርጎ እንዳሻው ማዘዝ ወይንም አመቺ ሆኖ ካገኘው ድምጥማጣቸውን ከራዲዮ መምሪያ ማጥፋት ፣ ድምፃቸው ከአየር ላይ እስከ ዘለቄታው እንዲሰረዝ ማድረግ ፍላጉቱ ነበር። የገዳሙ ምኞት ከደርግ 'መኢሶንና ኢህአፓ'ን ማጥራት ዘመቻ የውስጥ መመሪያ ጋር ተገጣጥሟል። እርግጠኛ ነኝ አበራ ይህን ጠንቅቆ ያውቃል። እውን ማን ይሙት ገዳሙ አብርሀ የነ ለገሰ አስፋውን ሙሉ ይሁንታ ሳያገኝ እነ አበራን ያውም ከሰራተኛ እና አሰሪ ህግ ወጭ ፎቶ በየበሩ ለጥፎ ከስራ ማገድ ብቻ ሳይሆን ወደ ቅጥር ግቢ ዝር እንዳይሉ አደረገ? የገዳሙ ፍላጎት የደርግም ጭምር ፍላጎት ነበር እናም አላንዳች ግርግር ተፈፀመ። የገዳሙ ድርሻ መመሪያን በማስፈፀም ሳይቆጠብ በግሉ የመረጠው ርህራሄ የጎደለው አፈፃፀም የደርግን ሚና አሳንሶ ሳያሳይ አልቀረም። እነ አበራ ከስራ የተባረሩት ግን በደርግ ሙሉ ፍላጎት ብሎም አፈፃፀሙ ደርግን ጭምር በሚያረካ መልኩ ነው። ባይሆንማ ኖሮ ገዳሙ እንዲህ ደረቱን ነፍቶ ግፍ ለመፈጸም ባልከጀለ ነበር።

ገዳሙ ምኞቱን ለማስፈፀም የደርግን ወቅታዊ መመሪያ ጥሩ አድርጎ ተጠቅሞበታል። ገዳሙ የኤርትራ ተወላጅ ስለነበር ለተገንጣይ ቡድኖች ይሰራ ነበር? በውነቱ አፉን ሞልቶ የሚያስተባብልም የሚመሰክርም ያለ አይመስለኝም። ሰውየው በሙያው ብቁ በባህሪው ግን ግትር ፣ አክብሩኝ ባይ እንዲሁም ከኔ በላይ አዋቂ የለም ብሎ የሚኮፈስ እንደነበር ከብዙ ጋዜጠኞች አንደበት ሰምቻለሁ። እንዲህ ያለ ስንቱን እናውቃለን?

በመጨረሻም በዓሉ ግርማን ማን ገደለው? የሚለው ጥያቄ አልተፈታም ፣ አልታወቀም የሚለው ጉዳይ በጣም ያሳዝነኛል። እውን በዓሉን ማን እንደገደለው አናውቅም? ወይንስ ማን አንደገደለው 'አታውቁም' እየተባልን እነ እገሌ እነ አገሌ ሳይሆኑ አይቀርም የሚል እንዲህ እንደ አበራ አይነት ዝባዝንኬ ስናመነዥግ እንድንቆይ የተወጠነ ሴራ አለ?

በዓሉንማ የበላው ደርግ የሚባል ዥብ ነው። መንግስቱ ሀይለማርያም ያውቅ ነበር? እንዴታ - አለበለዚያማ በምክትል ሚኒስትርነት ሹሞ ሲያበቃ የደረሰበት ሲጠፋ ሰራተኛዬን የት አደረሳችሁት ብሎ ይጠይቅ አልነበር? በዓሉ የተገደለው ኦሮማይን በመፃፉ ብቻ ነው። ያንን ፅሁፍ አርቅቆ አሳትሞ ለአንባቢ ሲያደርስ መዘዝ እንደሚከተል በዓሉ ጠፍቶት አይመሰለኝም። ጀግና ፣ አዋቂ እና ልበ ሙሉ ስለነበር የፈፀመው ይመስለኛል። ኦሮማይን አሳትሞ ከደርግ ጋር እንደወትሮው ተለሳልሼ ቀጥላለሁ ብሎ ይገምታል ብዬ አላስብም። ዛሬ በወያኔ አስራ ስምንት ዓመት ተፈረደበት ቃሊቲ የሚማቅቀው ጀግና እስክንድር ነጋ ለእውነት እና ለሰብአዊ ክብር በመቆሙ መራር መስዋዕትነት ሊከፍል እንደሚችል ጠፍቶት እንዳልሆነ ሁሉ።

ሙሉጌታ ሉሌ በተለያየ አጋጣሚ ሲገልፅ እንደሰማሁት አንዳንድ ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮች ሲኖሩ ጋዜጣዊ አቀራረባቸውን በሚመለከት መመሪያ ለመቀበል ወደ መንግስቱ ቢሮ ይጠራ ነበር። ይሄ ይፋ የሆነ በስራው አጋጣሚ ሊፈፅመው የሚጠበቅበት ግዴታ ነው። ዘግይቼም ቢሆን ወደ ጋዜጠኛ አለም የገባሁት እኔም የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ሙያዊ አፈፃፀምን በሚመለከት መንግስቱ ድረስ ባይሆንም እነ ሽመልስ ማዘንጊያ ፣ ዛሬ የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ ባለስልጣን ወደ ሆኑት የዚያን ጊዜው የደርግ ፕሬስ ጉዳይ ሀላፊ ወ/ሮ ሳህለ ወርቅ ዘውዴ ቢሮ ብዙ ተመላልሻለሁ። መንደር ምስረታን በሚመለከት ፣ ኢህድሪ ምስረታን በሚመለከት ፣ ወደ ሰሜን ጦር ስዘምት ባልስልጣናቱ ፊት ቀርበን መመሪያ ስንቀበል ነበር። ይሄ የተለመደ አሰራር ነው።

በነገሬ ላይ በአስራሰባቱ አመታት የደርግ ዘመን ያለፈኝ ዘመቻ አልነበረም። ጊዜና ቦታ ከክፉ ዕጣዬ ተገጣጥመው የተነሳ አስረኛ ክፍል በመሆኔ ዕድገት በህብረት ፣ ሁዋላ ደግሞ መሰረተ ትምህርት ፣ ዩንቨርሲቲ ገብቼ ለመመረቅ ሁለት ወር ሲቀረኝ መተከል የመልሶ ማቋቋም ዘመቻ ፣ በመጨረሻዎቹ የደርግ ዘመናት ደግሞ አንዴ ኤርትራ ሁዋላ ወሎ ሰሜን ሸዋ እና አሰብ ጦር ግንባር በመዝመት እነደ ማንኛውም ዘማች 'ወታደር' ጦሩ ሲበተን እኔም አዲስ አበባ በጥገኝነት ወደ ተከራየሁበት ቤቴ ተመልሻለሁ - ሁዋላም ተሰድጃለሁ። ላንገቴ ማስገቢያ ጎጆ ቤት እንኳ ያልነበረኝ ሰው ካንዱ ዘመቻ ወዳንዱ ስራወጥ ዘመኔን ጨርሻለሁ። ዝርዝሩን ለመግለፅ እዚህ ቦታው

አይደለም እንጂ በደረስኩባቸው ጦር ግንባሮች ሁሉ በተለይ የአካባቢ ሚሊሻዎች ወያኔን ለመመከት ያደረጉትን ተጋድሎ እያንዳንዱ ዜጋ ለአገሩ አንድነት ሲል ሲከፍል የቆየውን ከባድ መስዋትነት ለመመስከር በወደድኩ።

አበራ ጦር ግንባር መዝመቱን ደጋግሞ ጠቅሷል - ውነት ነው። በሆነ የስራ አጋጣሚ አንበሳ አውቶቡስን ወክሎ ኤርትራ በመጣበት ግዜ አስመራ ተገናኝተን ብዙ ተጨዋውተናል። ዛሬ ከሚያብጠለጥለው ከያኔው አንጋፋ የሙያ መሪ አስተባበሪያችን (አዝማቻችን) ሙሉጌታ ሉሌ ጋርም በቅርብ ሲያወጉ እንደነበር አስታውሳለሁ።

በአበራ ፅሁፍ ውስጥ አንድ ሌላ ያሳዘነኝ ነገር ቢኖር ወረድ ብሎ 'ሙሉጌታ ሲመኝ የነበረውን ምክትል ሚኒስትርነት ቦታ በማጣቱ በብስጭት ታሞ ለህክምና ወደ ውጭ አገር ሄደ' ይለናል። በውነቱ ወቅቱን በጣም አስታውሳለሁ - ደርግ አዲስ የካቢኔ ለውጥ ባደረገበትና መርዕድ በቀለ ምክትል ሚኒስትር ሆኖ በተሾመበት አካባቢ ሙሉጌታ ሉሌ ህመም ላይ ሆኖ ጳውሎስ ሆስፒታል መተኛቱን አውቃለሁ - ተመላልሼም ጠይቄዋለሁ። ውጭ አገር ለህክምና ሄደ የሚለውን አሉባልታ አበራ ከየት እንዳገኘው አላውቅም።

ይህን መጣጥፍ ለማርቀቅ ያነሳሳኝ በዓሉ ላይ ከተፈፀመው ግፋዊ ግድያ ጋር ተዳብሎ የቀረበው ነገር ግን ምንም ተዛማጅነት የሌለው በከፊልም ቢሆን በቅርብ በማውቃቸው ግለሰቦች ላይ ያነጣጠረ የግል ቂም ብሶት ሆኖ ስላገኘሁት ብቻ ነው። ከበዓሉ ኢፍትሀዊ አፈና ግድያ 'ትንታኔ' ጋር አያይዞ አበራ ከስራ ገበታው በግፍ መባረሩን ሰፊ ገፅ ሰጥቶ ማውሳቱ ወቅታዊም ተገቢም አደለም። አበራ ከስራ ገበታው የተባረረው በ1972 ዓም ግድም ሲሆን ደርግ በዓሉን የገደለው በ1977 ነበር። እንዴት አድርጎ የራሱን ከስራ መባረር ከአምስት ኣመታት በሁዋላ ከተፈፀመው በዓሉ አሟሟት ጋር ለማስታከክ እንደተነሳ ወይንም እንደ ተዛማጅ ጉዳይ ባንድ ሁተታ ማካተት እንደፈለገ ለመገንዘብ ይቸግረኛል። በዚህ አድራጎቱ አበራ ሊያፍርበት ይገባል።

እኔ በግል የማውቀው አበራን ብቻ ሳይሆን በፅሁፉ ያነሳቸውን ከስራ የተባረሩትን ጋዜጠኞች ፣ ለምሳሌ ፀጋዬ እንደሻውን ተፈራ አስማረ አብሬ ሰርቻለሁ ፣ አውቃቸዋለሁ - አፈር ይቅለላቸው። አቶ ሙሉጌታ ሉሌንም በጣም በቅርብ አውቀዋለሁ - አብሬው ሰርቻለሁ። እጅግም አድርጌ አደንቀዋለሁ። አቶ ሙሉጌታ ሉሌ በሙያው የተራቀቀ ፣ በአስተዳደር ችሎታው የላቀ ፣ በውነቱ በባህሪው ደግ እና ለሰው አዛኝ መሆኑን አፌን ሞልቼ እናገራለሁ።፡አቶ ሙሉጌታ ሉሌን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት አራተኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ እሱ ጋዜጠኛ ሆኖ ትምህርት ቤታችን ለስራ ጉዳይ በመጣበት አጋጣሚ ነው። ይህን ታላቅ ጋዜጠኛ በቅርብ ለመተዋወቅ ዕድል ያገኘሁት በእርሱ አስተባባሪነት ሰሜን ጦር ግንባር በዘመትኩበት ወቅት ነበር። አብረን በቆየንባቸው ስድስት ወራት እንደ አለቃ ሳይሆን እንደ ተማሪ ፍፁም ትሁት ሆኖ ነበር ያገኘሁት። አንድ ፅሁፍ አርቅቆ ሲያበቃ ቢሮው ጠርቶ 'አንተ ጎረምሳ እስቲ ይቺን ፅሁፍ አይተህ አርምልኝ' ብሎ እኔን ትናንት ጋዜጠኛ የሆንኩትን ሰው ዝቅ ብሎ ይጠይቀኝ ነበር። ፅሁፉን ለማረም ሳይሆን አንብቤ አፃፃፍ ስልቱን ለመቅሰም ስል ጊዜ ይወስድብኛል። ጋሽ ሙሉጌታ ተመለሶ ይመጣና 'እስካሁን አልጨረስክም? ብዙ የሚታረም ነገር አለው መሰለኝ' ብሎ ይጠይቀኛል። ፅሁፉን ካለ አንዳች እርማት ስመልስለት 'እንዴ አላነበብከውም ማለት ነው? አስቸኮልኩህ እንዴ?' ይለኛል። ይህን ትሁት ሰው ከባህሪው ጋር ፍፁም በማይገናኝ በማይጨበጥ ተራ አሉባልታ መክሰስ ዛሬ ማንን እንደሚጠቅም አላውቅም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ 'እባክህ አንዳንድ ነገር ፃፍ' እያሉ ከሚጎተጉቱት አንዱ እኔ ነኝ። ከብዕር አጣጣሉ ፣ በህይወት ዘመኑ ከመረመራቸው መፃህፍት ፣ ካነጋገራቸው ዜጎች የሚያካፍለን ብዙ በጣም ብዙ ልምድ እንዳለ አውቃለሁ። አዲስ አበባ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ባለው ቤተ-መፅሀፍ የምታገኟቸው ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ መፃህፍት እኔ እስከማውቀው ድረስ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ አልነበረም።

አበራ ሆይ ታላቁን ሰው በዓሉን የበላው ደርግ ነው ፤ አንተንና ባልደረቦችህንም ከስራ አግዶ ለእንግልት ያጋላጠው ይኸው ደርግ ነው። ውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የግል ቂም አርግዞ ጭብጥ ለማድበስበስ መሞከር ግምት ላይ ከመውደቅ በላይ ፋይዳ የለውም። በሙያችን ለአገር የጠቀምን መስሎን ከግል ምቾት እና ፍላጎት በላይ አፍላ እድሜአችንን ቆላ ደጋ ሮጠን በህልውና እንድትቆይ የተመኘንላት አገር ዛሬ እነዳልሆነ ሆናለች። አንተም ሁላችንም እንደምናውቀው የኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅ ዘብ ቆሞ የነበረው ከድሀው ህዝብ የተገኘ ሰራዊት የገበረው ደም ከህሊና ግምት በላይ ነው። ይህ አልበቃ ብሎ ዛሬ የሆነ ያልሆነውን ለመቀባጠር እና በወገን መካከል ጥረጣሬ ለማሳደር ቀላጤ ማርቀቅ ተገቢ ነው ብዬ አልገምትም። ይልቁንም የዕድሜ ብቻ ሳይሆን የሙያ እና ልምድ ባለፀጋ የሆኑ እንደ ሙሉጌታ ሉሌ ያሉ ዜጎች በመጠሪያ ዘመናቸው ስደተኛ ሆነው ፈተና መቀበላቸው ሊቆረቁረን ሲገባ ሌላ ሴራ መጎንጎኑ በማናቸውም መለኪያ ተገቢ አይደለም። አንተን ጨምሮ (ስደቱን ትተኸው አገር ገብተህ እንደሁ እንጃ?) ሙሉጌታ ሉሌ እና እኔ ዛሬ ጊዜውና አቅሙ ከተገኘ ልናተኩርብቻው የሚገባ እያሌ ቁም ነገሮች አሉ። እግር የወጋ እሾህ ስራ ያስፈታል እንዲሉ ስራ ፈትተህ ብዙ ሰው ስራ አስፈታህ።